በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በግብርና ሚኒስቴር የወጣ መመሪያ ቁጥር 456/2013

Directive Issued by the Ministry of Agriculture of the Federal Democratic Republic of Ethiopia No. 456/2021

| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ አስገብቶ የማባዛትና መልሶ የመላክ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 456/2013 | Directive for import and multiplication of unregistered varieties exclusively for re export Directive Number 456/2021 |

መግቢያ

በአገር ውስጥ ያልተመዘገበ ዝርያን በአገር ውስጥ ተመርቶ ለውጭ አገር ገበያ የሚቀርብበትን በተመለከተ ግን እንደ አስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ በሚወጣ መመርያ እንዲወሰን የተደነገገ በመሆኑ፤

Introduction

Whereas, it is declared that the ministry shall issue a directive that govern the process of production and export of seed of unregistered varieties as deemed necessary;

ዘር አምራቾች በአለም አቀፍ የዘር ንግድ ገበያ ውስጥ ለመግባትና ውጤታማ ለመሆን ገበያው የሚፈልጋቸው ምርቶች በብዛትና በጥራት ይዘው መቅረብ ግድ ስለሚላቸውና በአገር ውስጥ የተመዘገቡና የተለቀቁ ዝርያዎች ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ላለው ፍላጎት የሚመጥኑ ባለመሆናቸውና ተወዳዳሪነታቸውም ዝቅተኛ በመሆኑ፤

Where, as varieties that are registered and released at national level are not competent enough to meet global market demand which negatively affect seed producers to engage and be effective in global market to supply the required quality and quantity.

የባለሃብቶች በዘር ማምረት መሳተፍ የሥራ ዕድል የሚፈጥርና የውጭ ምንዛሪ ግኝት የሚያሳድግ በመሆኑ፤

Whereas,the engagement of investors in the seed production will contribute in creating employment opportunities and generating foreign currency;

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 17 እና በዕፅዋት ዘር ደንብ ቁጥር 375/2008 አንቀጽ 18(2) (ለ) አንቀጽ 34 (1) በተደነገጉት መሠረት ሚኒስቴሩ ይህን መመርያ አውጥቷል።

Therefore, in accordance with Article 17 of the Seed Proclamation No.782/2013 and Article 18(2) (b) and Article 34(1) of the Seed Regulation No.375/2016, the Minister has issued this directive.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

፩/ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ አስገብቶ የማባዛትና መልሶ የመላክ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 456/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል።

1. Short Title

   This directive may be cited as "Directive for import and multiplication of unregistered varieties exclusively for re export No. 456/2021"

፪/ ትርጓሜ

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና በዘር ደንብ ቁጥር375/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት

2. Definitions

   Whereas terms and phrases defined in the Seed Proclamation No.782/2013 and Seed Regulation

ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ:-

ሀ/ "በአፈር ላይ ያልተመረተ" ማለት ለዘር ብዜት የሚገባው ዘር ከአፈር ጋር ቀጥተኛ ንክኪነት ሳይኖረውና ከዕፅዋት ተባይ ተሸካሚ ነጻ ሆኖ የተመረተ ማለት ነው፤

ለ/ "ዕፅዋት ተባይ ተሸካሚ" ማለት አንድ ተባይ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ለመጓጓዝ የሚያስችለው አካል ነው።

ሐ/ "የዕጽዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት": ማለት አግባብ ያለው አካል ለዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ማለት ነው፤

መ/ "ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከለ የዕጽዋት ዝርያ": ማለት በዕፅዋት ኳራንታይን ሕግ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከሉ የዕፅዋት ዘሮችን ይመለከታል፤

ሠ/ "አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር " ማለት በግብርና ሥራ የተሰማራ ሆኖ ኃላፊቱ በተወሰነ በግል ማህበር ወይም በሽርክና ያልተመዘገበ ሰው ነው፤

ረ/ "ያልተመዘገበ ዝርያ" ማለት በአገሪቱ የዕፅዋት ዝርያ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ያልሰፈረ ዝርያ ማለት ነው።

ሰ/ "ጥብቅ ግብርና" ማለት ተለይቶ በሚታወቅ አካባቢ በዘር ምክንያት ስለ ሚፈጠር አሉታዊ ተጽዕኖ በተቆጣጠረው

No. 375/2016 shall have the same meaning, in this directive unless the context requires otherwise:

a) "Not produced on soil" means seed imported for seed multiplication shall not be in direct contact with the soil and being free from plant pests;
b) "Plant pest carrier" means any thing that can serve as a crrier of pest from one place to another.
c) "Phytosanitary certificate" means a certificate issued by the relevant authority attesting the health of plants.
d) "Plant variety prohibited from entry" means varieties prohibited from entry into the country in accordance with the plant quarantine law;
e) "Small holder farmer" mean a person who engaged in agriculture but not registered as Private Limited Company (PLC) or Share Company;
f) "Unregistered Variety" means a variety that is not registered in the country's variety registry book.
g) "Confined agriculture" means an agriculture conducted under close

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry Of Agriculture

አካል ክትትልና ቁጥጥር የሚካሄድ ግብርና ነው።

supervision and control, for any negative impact by the regulatory body in a designated confined area.

፫/ የተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው ከውጭ አገር የመጡ ያልተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች መነሻ ዘሮች አገር ውስጥ በጥብቅ ግብርና እንዲባዙና ወደ ውጪ ለመላክ በተፈቀደላቸው የዕፅዋት ዝርያዎች ዝርዝር በተገለጹት ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል። እነዚህ ዝርያዎች ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር መሰረት የሚገለጽ ይሆናል።

**3. Scope**

Notwithstanding the provisions of the seed proclamation, this directive shall be applied on imported early generation seed of unregistered varieties permitted for multiplication in confined agriculture exclusively for re export purposes. The list of these varieties shall, on a regular basis, be made public by the Ministryf/

፬/ የመመሪያው ዓላማ

በውጭ አገር ገበያ ላይ ተፈላጊነት ያላቸውና በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ከውጭ የሚመጡ የዕፅዋት ዝርያዎች በአገር ውስጥ መመዝገብ ሳያስፈልጋቸው የሚባዙበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለውጭ ገበያ ብቻ እንዲቀርቡ በማድረግ አገሪቱ ከውጭ ንግድ ያላትን ተጠቃሚነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ ነው።

**4. Objective**

To ensure sustainable improvement of the Country`s benefit from foreign trade by allowing import of unregistered varieties with high global market demand without being registered locally and create conducive environment for their multiplication and exclusively for re export.

## ክፍል ሁለት

## ዝርያዎች ለማስገባትና ወደ ውጪ ለመላክ መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

፭/ ያልተመዘገበ ዝርያን ለማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡

ሀ/ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው ለጥብቅ ግብርና የሚሆን መስፈርት ማሟላቱ ተረጋግጦ ያልተመዘገበ ዝርያን አባዝቶ ወደ ውጪ ለመለክ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

ለ/ ከሚኒስቴሩ የማስገቢያ ፈቃድ ያገኘ፤

ሐ/ ከመነጪበት አገር ዝርያው ስለመመዝገቡ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤ሆኖም ያልተመዘገበ ከሆነ የአገሪቱን የምዝገባ ሥርዓት ማለፍ ይኖርበታል፤

መ/ ከጭነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የግዥና የርክክብ ሰነድ ማያያዝ የሚችል፤

ሠ/ የዕፅዋት ኳራንቲን፣ የደህንነት-ህይወትና ብዝሃ ህይወት የሚጠየቁትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

## PART TWO

## REQUIREMENTS FOR IMPORTING AND EXPORTING VARIETIES

5. **Any person to import unregistered variety shall:**
   a) have competence certificate granted by the ministry to multiply and export unregistered variety up on fulfilling the Ministry requirements for confined agriculture;
   b) acquire import permit from the ministry;
   c) submit document attesting its registration in the country of origin; otherwise, it shall undergo the national registration proceedures,
   d) attach procurement and delivery documents in relation to the shipment;
   e) fulfill quarantine, bio safety, and biodiversity;requirements

## ክፍል ሦስት

## የማባዛት ሂደት አፈጻጸም

፮/ የተፈቀደ ያልተመዘገበ ዝርያን ያስገባ ማንኛውም ሰው ያስገባውን ዝርያ የራሱ ወይም በሌላ አልሚ ማሳ ላይ ተቆጣጣሪው አካልን በማሳወቅ በውል ላይ ተመስርቶ በጥብቅ ግብርና ማባዛት ይችላል፡፡

፯/ በአንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያልተመዘገበ ዝርያን ከውጭ አገር ያስገባ ማንኛውም ሰው በሌላ አልሚ ማሳ የሚያባዛ ከሆነ የብዜት ሂደቱን ሙሉ በሙሉ በጥብቅ ግብርና መካሄዱን አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተረጋገጠ የውል ስምምነት ሰነድ ማቅረብ የሚችል::

፰/ ያስገባውን ዝርያ በኮንትራት ስምምነት ጥብቅ ግብርና ባልሆነ ሁኔታ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ ማባዛት አይችልም፡፡

፱/ ያልተመዘገበ ዝርያ ዘር የተባዛበት ማሳ ለሌላ ተግባር ከመዋሉ በፊት አፈሩ ከዘር ጋር በተያያዘ የመጣ የዕጽዋት በሽታና ተባይ ነጻ ስለመሆኑ በተቆጣጣሪው አካል መረጋገጥ አለበት፡

## PART THREE

## MULTIPLICATION PROCESS

6. Any person who has imported permitted unregistered variety shall multiply the variety in his own farm or on the contracted farm of another investor, through confined agriculture, notifying the regulatory body.
7. Notwithstanding the stipulation under Article 6 above, any person, who imported unregistered variety to multiply on another investor`s farm, shall submit acontract agreement approved by a disgnated regulatory authority that assures the multiplication process is done under confined agriculture.
8. Importers shall not multiply unregistered varieties on farmer's field, unless & otherwise it is done under confined agriculture supported by contractual agreement.
9. Before using the farm that has been used for multiplication of unregistered variety for other purposes, it shall be approved by the regulatory body for being free from seed-borne pathogens and pests resides in the soil;

፲/ ዝርያው ስምምነት ከተደረሰበት ማሳ ውጭ ሲባዛ ቢገኝ አግባብ ባለው በሀገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ ለመሆን ሃላፊነት የሚወስድ መሆን መቻል አለበት፡፡

10. The person shall be accountable by the relevant law of the country, if the unregistered variety is multiplied on a farm other than the agreed one;

፲፩/ ያስገባውን ዝርያም ሆነ ከዝርያው የሚገኝን ምርት ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ወይም ገበያ ላይ እንዲያውለው. በሽያጭም ሆነ በስጦታ አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

11. Importer of unregistered variety shall not give to another person, to use or market, the imporeted variety or any product thereof by way of sale or gift.

፲፪/ያልተመዘገበን ዝርያ ተረፈ ምርት ዘር ያለው ከሆነ ለሰው ለምግብነትም ሆነ ለእንስሳት መኖ ግልጋሎት በማንኛውም መልኩ በአገር ውስጥ በሽያጭም ሆነ በስጦታ ጥቅም ላይ መዋል አይችልም፡፡

12. If the by-product of unregistered variety has seed, it shall not be given or sold to be used in the country for human consumption or livestock feed in any form.

፲፫/በአንቀጽ 12 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተረፈ ምርቱ ዘር ያለው ከሆነ የተገኘውን ምርት በጥብቅ ግብርና ማሳው ተቀጣጣሪውን አካል በማሳወቅ ጥቅም ላይ ማዋል ይችላል፡፡ ሆኖም ጥቅም ላይ የማይውል ከሆነ ተቆጣጣሪ አካል በሚሰጠው ምክረ-ሃሳብ መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

13. Notwithstanding the stipulation under article 12, if the bi-product contains seed, the product may be used to reproduce in confined agriculture upon notifying the regulatory body. However, if it can't be reused, it shall be removed based on the advice of the regulatory body.

፲፬/ ያስገባውን ዝርያ በሚያባዛበት ሂደት ውስጥ በተገባው ውልና ስምምነት መሰረት እያባዛ መሆኑን አግባብ ላለው የመንግስት የቁጥጥር አካል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

14. In the process of multiplying the imported variety, he shall notify the relevant regulatory body that the multiplication is on-going according to the agreement.

## ክፍል አራት
## የተባዛን ዝርያ ወደ ውጭ የመላክ ሂደት አፈጻጸም

፲፭/ ያልተመዘገበን የዕፅዋት ዝርያ በአገር ውስጥ አባዝቶ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሊኖረው ይገባል፡፡

፲፮/ ተቀባዩ አገር የሚጠይቀው የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ቢኖር ይህንን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይገባል፡፡

፲፯/አምራቹ የጥራት ማረጋጋጫ ሰርተፍኬት ከፈለገ በሀገሪቱ አሰራር መሰረት መጠየቅና ማግኘት ይችላል፡

፲፰/ አምራቹ የተባዛው ዘር ወደ ውጭ ገበያ መላኩን ለሚኒስቴሩ ማስረጃ ያቀርባል፡፡

## PART FOUR
## THE IMPLEMENTATION OF EXPORT PROCESS OF UNREGISTERED VARIETY

15. Any person shall have a competency assurance certificate to multiply and export unregistered variety.
16. If any phytosanitary certificate is required by the recipient country, the exporter shall get competency of certificate from designated body;
17. If the producer wishes to have a quality assurance certificate, he may request and shall be granted in accordance with the procedure of the country.
18. The producer shall provide documents to the ministry confirming the multiplied seed has been exported.

## ክፍል አምስት
## የሚኒስቴሩና ተባባሪ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

### ፲፱/ የሚኒስቴሩ ሃላፊነትና ተግባር፡

ሀ/ ይህን ተግባር ሃላፊነት ወስደው ያልተመዘገበ ግን በአገር ውስጥ ተባዝቶ ወደ ውጭ የሚላክን ዝርያ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማባዛት እና ወደ ውጭ ለመላክ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

ለ/ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው የዕፅዋት ዝርያ የአገሪቱ የኳራንታይን ሕግን አሟልቶ መገኘቱን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች በአፈር ላይ ያልተመረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

መ/ አምራቹ በሚጠይቀው የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ መስፈርት መሰረት ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

ሠ/ እንዲባዛ የተፈቀደው ዝርያ ለተፈቀደለት ዓላማና ተግባር መዋሉን ቁጥጥርና ክትትል ያደረጋል፤ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ውሎ ሲገኝ በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 በሚደነግገው መሰረት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

## PART FIVE

## DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE MINISTRY AND COLLABORATORS

### 19. Duties and Responsibilities of the Ministry

a) Issues Certificate of Competence for those who take responsibility to import, multiply and re export unregistered varieties;

b) Ensures imported of unregistered varieties fulfill the plant quarantine requirements of the country;

c) Ensures unregistered varieties to be imported are not produced on soil;

d) Issues phytosanitary certificate as per the request of the producer;

e) Follow and regulate permitted unregistered variety for multiplication is used according to the intended purpose; if used outside the intended purpose, the ministry shall ensure legal measures are taken as per the seed proclamation No782/2013;

ረ/ የተመረተው ዘር ወደ ውጭ መላኩና ተረፈ ምርቱ በተገቢው መንገድ መወገዱን ያረጋግጣል፡፡

**፳/ የተባባሪ አካላት የትብብር ማዕቀፍ**

የአከባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ፣ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት፣ የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት፣ንግድና ኢንዱስትሪ፣ ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች እና በየክልሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በትብብር ይሠራሉ፡፡

**፳፩/ መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ 20 ቀን 04/2011 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ዑመር ሁሴን

ግብርና ሚኒስትር

f) Ensures produced seed is exported and the by-product is removed properly.

**20. for Collaborators Cooperation**

Environment protection, Forest, and Climate Change; Coffee and Tea Production and Marketing, Ethiopian Biodiversity; Trade and Industry; Investment offices and the relevant regional bodies will cooperate for the enforcement of this directive based on respective powers and responsibilities vested upon by law.

21. Effective Date

This directive shall be effective from 29th day of December 2019.

Umer Hussien

Minister of Agriculture